የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ግንቦት 2 2001 ዓ.ም

# 'ትግል እንዴት?' ጥያቄ የሚመለሰው በተጨባጩ ሁኔታ ነው

ለሀገሩና ለመብቱ መታገል የሚገደድ ህዝብ በቅድሚያ ማንን መታገል እንዳለበት ማለትም ጠላቱ ማን እንደሆነ ማወቅ ይኖርበታል፡፡ ተደጋግሞ እንደተገለፀው ጠላትና ወዳጅን ያልለየ ትግል ወዳጁን ጠላት ብሎና በግልባጩም ጠላቱን ወዳጅ አድርጎ በምሳሌያችን እንደሚባለው "ወርቅን በጭቃ ነብርን በጫንቃ" ተሸክሞ ራሱን መጉዳትን ያስከትላል፡፡

ጠላቱን ያወቀና የራሱንም አቅም በትክክል የተገነዘበ በፍልሚያው ብዙውን ጊዜ አቸናፊ ይሆናል፡፡ ጠላትን ማወቅ ሲገባ ጠላትንም እንዴት መታገል መረዳት ደግሞ በጣም ወሳኝ ነው፡፡ በሀገራችን ተቃዋሚ ኃይሎች ዘንድ ለረጅም ዓመታት በትግል ስልት ወይም ይዘት ላይ ደረቅ ክርክር በወፍ ቋንቋ ሊባል በሚችል ደረጃ ሲካሄድ ቆይቷል፡፡ በቅድሚያ በደፈናው ሰላማዊ የተባለው ትግል ከሌላው በተለይም ብረትን ከማንሳት ትግል ጋር ከቶም ሊገናኝ የማይችል አድርገው የተረዱት ክፍሎች አንድም ሰላማዊ ትግልን አገዛዙ በሚፈቅደው መሰረት በየጊዜው በምርጫ በመሳተፍ ደረጃ ፈርጀው ከዚህ ጎዳና ሌላ ሁሉም ወደ እንጦርጦስ ያነጉዳል ብለው በመደምደም ስህተትን ሲያስተጋቡ ተደምጠዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ይህ ሰላማዊ ትግል በሚለው ጥቅል ስም የሚቀርበው የትግል አማራጭ በተለይም ሕዝባዊ አመፅን ያቀፈና ከሶዌቶ እስከ ኢንቲፋዳና እስከ ግንቦት 97 ያለውን ትግልና አመፅ የሚያንፀባርቅ መሆኑን መገንዘብ የተሳናቸው ክፍሎች የሕዝብን መነሳሳትና አመፅ እንደ መርገምና መዓት በመውሰድ ከአገዛዙ ባልተናነሰ "ሁኔታው እንዳይበላሽ" ብለው ፀረ አብዮት ፀረ ለውጥ እሳት አደጋ መከላከያ ሚናን ይላበሳሉ፡፡ በ1997 ዓ.ም በእንጭጩ የተቀጨውን የሙት ከተማ አድማ ያስታውሷል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ የትጥቅ ትግል መንገድ ያዋጣል ባዮች በሕዝባዊ አመፅ ረገድ ሊገኝ የሚችለውን ድል በማንኳሰስ ሰፊ የሕዝብ መነሳሳትንና አመፅን ማዘጋጀት ክብደት ያለው ስምሪት መስሎ አይታያቸውም፡፡ ሁሉም ፅንፎች የትግሉን ክብደት ሲቀንሱና በጎጂ ደረጃ ውዥንብርን ሲያሰፍኑ እያየ  ሲሆን በተለይም በዚህም በዚያም ስልት የሚሉት በመረጡት ስልት የሚያደርጉት እንቅስቃሴ የነበዘ ወይም የደከመ--የፈዘዘ ከሆነ ደግሞ ጉንጭ አልፋ ክርክርና የመነቸከ ሰበካ ትግልን ተካ ቢባል ወቀሳው

ትክክል ይሆናል፡፡ የትግል ስልት ከሚዛኑና ዋና ይዘቱ አንፃር ሲገመገም ይዘቱን ወሳኝ የድርጅት ፍላጎትና የተወሰኑ መሪዎች ስሜት ሳይሆን ተጨባጩ ሁኔታ መሆኑ መታወቅ አለበት፡፡ መለስ ዜናዊና መሰሎቹ ብረት ባነሱትና በሚያነሱት ላይ ውርጅብኝና ክስ ስላሰሙ ብቻ ሽምቅ ተዋጊዎች ሽብርተኛ ናቸው ማለት አይደለም፡፡ ከታሪክ እንደምንማረው የአንዱ ነፃ አውጪ የሌላው ሽብርተኛ ነው፡፡ ማን ገምጋሚ፤ ማን ፈራጅ የሚለው ጥያቄ ወሳኝ ነው፡፡ ለነፃነቱ የሚታገለውን ሁሉ ፀረ ሕዝብ ኃይሎች ሽብርተኛ ማለታቸው የሚጠበቅ ነውና፡፡ ይህ በዚህ እንዳለ ግን ሁኔታው የግድ ሳይል ደግሞ ብረት ማንሳቱ ወይም በሰላማዊ መንገድ መታገሉ ቅድሚያ ሊሰጠው በሚችልበት ወደ ብረት አመፅ መሸጋገሩ ትክክል አይሆንም፡፡ ለማንኛውም ይህን ከዚህና ከዚያ ፅንፍ አጣብቂኝ ገብቶ መንቀሳቀሻ ውሉ እንዳይጠፋን ከተፈለገ በቅድሚያ ሰላማዊ ትግል ስንል በአገዛዙ ቁጥጥር ስር በሚካሄድ የምርጫ ድግስ በአጃቢነት መሰለፍ ማለት ሳይሆን ከሰልፍ እስከ ሕዝባዊ አመፅ ድረስ ያለውን የትግል ዘርፍ ሁሉ ያካተተ መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ሰላማዊ ሰልፍ ማዘጋጀት፤ የሥራ ማቆም አድማን ማካሄድ፤ የሙት ከተማን አድማ እውን ማድረግ፤ ኪራይና ግብር አንከፍልም ብሎ ማደም፤ የአገዛዙ ዕቅዶች ማደናቀፍ፤ ፀረ ሕዝብ እርምጃዎችን እንዳይወስድ ኃይሉን ማዳከም፤...ወዘተ ሁሉ የሚያካትት ቀጣይ የጋራ መነሳሳትና የአመፅ ክስተትን በጥቅሉ ሁሉን ያቀፈ ነው፡፡ ሰላማዊ ትግል ማለት በወያኔ አገዛዝ ምርጫ መሳተፍና ጠባይን አሳምሮ መገዛት ማለት አይደለም፡፡ ከወያኔ ህግ ተብዬ ድንጋጌ ውጪ ብቻ ሳይሆን በተፃረረ መንገድ የሚካሄድ ተቃውሞን ያመለክታል፡፡ ለዚህም ነው ሁለገብ ትግል ሲባል ከተማ ገጠሩ÷ ላባደሩና አርሶ አደሩ÷ ተማሪው ምሁሩ÷ የመንግሥት ሰራተኛው ታክሲ ነጂው÷ አስተማሪው÷ ወንዱ ሴቱ÷ ወጣት ሽማግሌው ባልቴቱ ሁሉ የሚሳተፍበት መሆን አለበትና ሕዝባዊ አመፅን አቀፍ ሰላማዊ ትግሉ ከትጥቅ ትግሉ ጋር መቀናጀትና መተሳሰር ያለበት፡፡ ትግል ስንል ሕዝብን አቀፍ መሆን አለበትናም ሕዝብን በተመልካች የሚመድቡ አቋራጮችና የሚወድቀውን በአዲስ ጨቋኝ የሚተኩ መፍትሄ ተብዬዎች ሁሉ ለትግል አይበጁም እንላለን፡፡ ይህም ማለት ያለውን አገዛዝ በመፈንቀል በሌሎች መኮንኖችና ምርጦች የሚተካ መፍትሄ ለሕዝብ አይበጅም፡፡ ሕዝብን ያላቀፈና ያላሳተፈ የምርጦችም የብረት ትግል ሊገፋ መቻሉ አጠራጣሪ ከመሆኑ ሌላ ከሕዝብ ከተነጠለ ወደ ሽብርተኝነት ማምራት ሊገደድ መቻሉም መሳት የለበትም፡፡

ዛሬ በኢትዮጵያ ያለው ተጨባጭ ሁኔታ ለብዙዎች ምስጢር አይደለም፡፡ በሥልጣን ያለው ፀረ ሕዝብ ቡድን በንፁሃን ደም ታጥቦ በምንም ዓይነትና መቼም ቢሆን የሕዝብን

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel . 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France

ድምፅ እንደማይሰማና እንደማያከበር ግልፅ አድርጓል። በማጅራቱ የሚታረድና ከዚህ ሁሉ ተመክሮ በኋላ የወያኔን አገዛዝ ወዳጅ ወይም ህግ አክባሪ ብሎ የሚገምት ካለ ለወያኔ ያደረ የተደናገረ ወይም ከማሰብ ችሎታ ጋር አምርሮ የተቆራረጠ ብቻ ነው። የመለስ አገዛዝ የምርጫውን ህግና ኮሚሽን ለራሱ በሚበጅ በቁጥጥሩ አስገብቶ እያለ ነፃና ፍትህዊ ምርጫን ለማግኘት መጠበቅ ልብ ድርቀት እንጂ ሌላ አይደለም--ፋይዳ ቢስ ነው። በመሆኑም ይህን አማራጭ ዛሬም እሹሩሩ ለማለት መነሳት በሕዝብ ትግል ላይ መቀለድ ነውና ከዚህ መንገድ ተጓዦች ጋር መሰረታዊ ልዩነት ይኖረናል ማለት ነው። በምርጫ አንሳተፍም ማለትም ትግል መሆኑ መረሳት የለበትም። በአገዛዙ ላይሁለገብ ማዕቀብ ማድረግና ቅንጣትም ትብብርን መንፈግ ትግል መሆኑም መዘንጋት አይገባውም። ለሕዝብ በማይፈይድና ከወዲሁ በወያኔ አሸናፊነት መደምደሙ በታወቀ ምርጫ ግቡ፣ እሰየው በርቱ ስህተትን ድገሙ የምንል ሳይሆን በማይሰድ በማይወስድ መንገድ ለመጓዝ ዳግም መጣሩ ትግልን ያጠፋልና ተዉት ነው የእኛ ምክር የሚሆነው። ጉዳዩ ወይም ችግሩ ግልፅ ነው። የግንቦት 1997 ተመክሮ አለ። ያኔ ተይዘው እስከዛሬ በእስር የሚማቅቁት ሺዎች አልተፈቱም። አገዛዙ ያደረገው ቀናና ይህ ነው የሚባል ለውጥ የለም። ዛሬ ከትላንት ብሷል፣ ከፍቷል። የመለስ ቡድን ምርኩዝ ምሰሶ አሁንም አፈናና ጭፍጨፋ ነው--ሀይል ነው፣ ነፍጥ ነው። ስለዚህም በተለምዶ አነጋገር የወያኔ አገዛዝ የሚገባው ቋንቋ ከትግርኛ ባሻገር ከጓንዴ እስከ ክላሺን ጥይቱ ሲንጣጣና የተናደደ ሕዝብ መፈክርን እያሰማ ሲተም ሲጮህ የሚደመጠው ነው። ራሱም የወያኔ አገዛዝ ቢሆን በብረት ያገኘነውን በሰላምና ዕርቅ አንሰጥምና ጫካ ግቡና ሞክሩን መንገዱን ጨርቅ ያድርግላችሁ፣ ጦርነት መሥራት የምንችለው እኛ ብቻ ነን ዋ ብሎ በዕብሪት ቢሆንም ድል በትግል ብቻ የሚለውን ሀቅ ሊነግረን ተገዷል። ስለዚህም ዛሬ የወያኔን አገዛዝ ከሥልጣን ማስወገጃው ዋናና ብቸኛ መንገድ ሁለገብ ትግል ነው።

የሕዝብ ክንድ መላላትና መዛል የለበትም። የሕዝብ ጎራ ከተከፋፈለ ወይም የሕዝብ የትግል ትኩረት በአንድ ዒላማ ላይ መሆኑ ቀርቶ በዚህም በዚያም ሆኖ ከተዘበራረቀ ትግል ድልን ሊቀዳጅ ይሳነዋል። ከዚህ አንፃርም ነው÷ ደጋግመን ለመግለፅ እንደሞከርነው÷ አንድም ጠላት ማነው በሚለው መሰረታዊ ጥያቄ ላይና በሌላ በኩል ደግሞ ዋናው የትግል ትኩረት/ስልት በሚለው ላይ የጋራ ግንዛቤ መያዙ በጣም አስፈላጊ የሚሆነው። በዚህ የምርጫ አማራጭ፣ በዚያ የሰላማዊ ትግል ወሽዋሻ አፋዊ "ትግል"፣ በወዲያ ደግሞ ትጥቅ ትግል እየተባለ በአራቱም አቅጣጫ መክነፍና አልፎም እርስ በርስ መላተም ከሰፈነ የወያኔ አገዛዝ ዕድሜው ይራዘማል። ለሕዝብ በሀቅ የሚታገሉ ኃይሎች

በበኩላቸው የማያዋጣ የትግል አቅጣጫን መተቸትና ሕዝብም እንዳይደናገር መምከር ማስጠንቀቅ ይገባቸዋል ብቻ ሳይሆን ግዴታቸው ነው:: ከዚህም የተነሳ በአሉታዊ ተተቸን ብሎም ተዘለፍን የሚሉ ካሉ ጉዳዩ የሕዝብ ትግል ዕጣ ነውና በዝምታ የሚታለፍ አለመሆኑ ሊገለፅላቸው ይገባል ማለት ነው:: የወያኔ አገዛዝ በምርጫዬ ካላጀባችሁኝ ህጋዊ ፈቃድን እነጥቃለሁ ማለቱ ራሱ ህገወጥ ውሳኔ መሆኑን መቃወም ያሻል እንጂ ፈቃዳችንን እንዳንቀማ በሚል ስጋት ብቻ ለወያኔ ሽፋን ሰጪ ሆኖ ትግልን መጉዳት አያስፈልግም:: ድርጅቶች የሚበጃቸውን የትግል ስልት (በሃቅ ሊታገሉ እስከወሰኑና እስከተነሱ ድረስ) የመምረጥ መብት ያላቸው ቢሆንም በበኩላችን በአሁኑ ተጨባጭ ሁኔታ ወያኔን መታገያው ዋናና ፍቱን ስልት ሁለገቡ ትግል ነው እንላለን:: ሁለገብ ትግል ስንልም በትጥቅ መታገልን (በገጠርም በከተማም) እንዲሁም በከተማም በገጠርም ሕዝባዊ አመፅን ማካሄድን ይጠቀልላል:: ሁለገብ ትግል እንዴት የሚለው ደግሞ ያለውን የሀገር ተጨባጭ ሁኔታ ከአካባቢውና ዓለም አቀፉ ሁኔታ ጋር አዛምዶ በመመርመር መፍትሄና መንገድየሚገኝለት ነው:: አንዳንዶች ሕዝብ የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን መብቱን በመንጠቅ አሜሪካወይም ምዕራቡ የኢትዮጵያን ዕጣ ፈንታ እንዲወስን አሳልፈው ስለሚሰጡ ሁለገብ ትግልን አሜሪካ ስለማይደግፍ አያዋጣም በሚል ይቃወማሉ:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ለራሱና ለህገሩ እንዴት መታገል እንዳለበት ወሳኝ ማንም ባዕድ ሊሆን ካለመቻሉ ሌላ ምዕራቡም ቢሆን አክብሮ መፍትሄ ፍለጋ የሚገባው የሚታገል ሕዝብ ሲያይ መሆኑን ከዳርፉር እስከ ዩጋንዳ፣ ከሞዛምቢክ እስከ ካሬን በርማ ያየነው ነው:: በቅርቡም የኔፓል ህገር ወዳዶች ትጥቅ ትግልም ሕዝባዊ አመፅም በተቀናጀ መልክ አካሂደው ምንም እንኳን ምዕራቡም ሆነ የአጠገባቸው ህንድ ብትቃወማቸውም ለሥልጣን በቅተዋል ::

ከዚህ ሌላ ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ በዓለም አቀፍ ደረጃ ፀረ ሙሶሊኒ ትግሉ ማላገጪያ ሲሆን ደጋፊ አጣን ብሎ ትግሉን አላቆመምና ያለን የራሳችን ታሪካዊ ቅርስ የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታግድ በሚለው የትግል ስልት ለመሰማራት የማንንም ፍቃድ ጠያቂ መሆን የለብንም የሚል ነው:: ስለዚህም የወያኔን አገዛዝ አስወግዶ ኢትዮጵያን ከጥፋት ለማዳን የሚቻለው፣ የሕዝብን ድልም ላለማስነጠቅ የሚቻለው በሁለገብ ትግል ተሰማርቶ ሕዝባዊ ኃይልን በማጠናከርና ለድል በማብቃት ብቻ ነው::

የኢትዮጵያ ሕዝብ ያቸንፋል!!

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France